# ይድረስ ለፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም
# ሀቅን ተናግሮ በመሸበት ያድሯል

እጅጉ ዓለምነህ

ወደ ጅብ ዋሻ ልገባ መነሳቴን አውቄዋለሁ ። በተለይ በአሁኑ ጊዜ አዋቂ፤ተዓምረኛ፤ ታላቅ መሪ ወዘተ በሚል በላያችን ላይ--እኛ ሳንመርጣቸው ወይም ሳንሰይማቸው --የተሰየሙ ግለሰቦችን መንካት መተቸት በሰፊውና በአያሌው የሚያስወግዝ ሆኖ ተገኝቷል ። ከነዚህ ክቡራን አንዱ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ናቸው ። ከትችት በላይ ናቸው ተብለው በአድናቂዎቻቸው ቅርስ ሊባሉ ትንሽ ቀርቷቸዋል ብል ትክክል ነው ። ግን ብዙውን ጊዜ የፕሮፌሰር መስፍን ሚናና እንቅስቃሴ የሚያስመስገናቸው ሳይሆን የሚያስወቅሳቸው መሆኑ መሸፋፈን የሌለበት ነው ። ስለሆነም ሀቅን ተናግሮ የሚመጣውን ውርጅብኝ ለመቀበል ዝግጁ ሆኛለሁና ይህን የሚከተለውን ጽሁፍ ለማቅረብ ተነስቻለሁ ። አባይን በጭልፋ ቢሆንብኝም ሌሎች እንዲጨምሩበት ሀገር ትጠይቃለች ። ሰኞ ወደ ለንደን መጥተው አዲስ መጽሃፍ አቀርባለሁ ባይ ናቸውና ሀገር ወዳዶች ሀቁን ነግረው በቃ ሊሏቸው ይጠበቃል ።

ፕሮፌሰር መስፍን መጽሃፍትን ለገበያ አቅርበዋል ። በትምህርታቸው በጂኦግራፊ ተወስነው ቢቆዩ መልካም ነበር የሚሉት አልተሳሳቱም ። ወደ ፖለቲካው መንደር ዘው ሲሉ ( ይህን ሲያደርጉም ቆይተዋል) የሚጽፉትም የሚያደርጉትም ከጥቅሙ ጉዳቱ አመዝኖ ይታያል ። በሶማሊያ ላይ ትምክህት አዘል ጽሁፍ አቅርበው ነበር ። አርበኞችን ሳይቀር በባንዳነትም ለመወንጀል ሞክረዋል ። አማራን በደፈናው የለም ብለው ሰርዘውታል ። እስቲ መለስ ብለን ሚናቸውን እንቃኘው ።

የዩኒቨርስቲ ተራማጅ ተማሪዎች የሰላም ጓድ /ፒስ ኮር/ የተባሉት አሜሪካኖች ሰላዮችና በተለይም የብሄረሰብን ልዩነት አራጋቢዎች ናቸው ብለው በከሰሱበት ወቅት  ፕሮፌሰር መስፍን ይህን የአሜሪካ ተቋም ደግፈው የቆሙት በወቅቱ ጓደኛቸው የነበረች ወጣት አሜሪካዊ (ሩዝ) ጋር ባላቸው ወዳጅነት ነው ተብለው ታምተው ነበር ። የፕሮፌሰሩ ቀጣይ ወዳጅነት ከአሜሪካ የጀመሩት በዚያን ጊዜ ነው ይባላል።

በ60 ዎቹ ዓመታት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በመንግስት ታግዶ የነበረውን ታገል/ስትራግል ይባል የነበረውን ጋዜጣ እንደገና ለማስጀመር አማካሪ ወይም ጋራንቲ ሁኑ ተብለው በተማሪዎቹ ተጠይቀው እምቢ በማለታቸው ከተማሪዎቹ ጋር ቀጣይ ሆኖ የቆየ ቅራኔን ፈጥረዋል

ንጉሱ ሊወርዱ ሁለት ዓመት ወይም ሶስት ዓመት ሲቀራቸው በአንድ ስብሰባ ላይ ተራማጅ ነኝ ብለው የንጉሱን አስተዳደር በመውቀሳቸው ንጉሱ ሕዝብን ወደድኩ ካልክ አንተው አሻሽለው ብለው የግምቢ አውራጃ አስተዳዳሪ አድርገው ሲሾሟቸው ንጉሱን በአማላጅ ለምነው ቀርተዋል ።

ፕሮፌሰር መስፍን የሰብዓዊ መብት ድርጅት መሰረቱ ሲባል ታዋቂው ፕሮፌሰር ስቬን ሩቤንሰን በኢትዮጵያ ተዓምር ታየ ብሎ አሹፎ ነበር ። ፕሮፌሰር መስፍን በመብት ጠባቂነት ሳይሆን በዱለኛነትና ለተለየ አቅዋም ትግስት አልባነት ይታወቁ የነበሩ ሰው በመሆናቸውና ለሰውም ንቀት አላቸው ይባል ስለነበረ ነው ።

በዘመነ ደርግ ፕሮፌሰሩ መኮንኖቹን ለመደገፍ ጊዜ አልፈጀባቸውም ። ከሻዕቢያው በረከት ጋር ሆነው የደርጉ የምርመራ ኮሚሽን አባል በመሆን የቀድሞ መንግስት ሚኒስትሮችንና ባለስልጣኖችን ቁም ስቅል ሲያሳዩ እንደነበር በነጻ ጋዜጦች በወያኔ ጊዜ በሰፊው ተጋልጧል ። መንግስቱ ራሱ በሰጠው ቃለ መጠይቅ “ፕሮፌሰር መስፍንን ምን እናድርግ ብለን ብንጠይቃቸው "(ደርጎች) ጠመንጃው በእጃችሁ አይደለም ወይ ብለው መልሰውልናል” ሲል አጋልጧል። ለሲቪሎች ስልጣን አትልቀቁ ብለው መምከራቸውንም አልተረሳም ። የመንግስቱን ቃል ማመን አያስፈልግም ብንል እንኳ የመርማሪ ኮሚሽን ሊቀ መንበር ሆኖ የተመደበ ሰው ተመርማሪዎቹ ምርመራቸው አልቆ ለፍርድ ባልቀረቡበት ሁኔታ በጅምላ በማናለብኝት ሲረሸኑ ለ17 ዓመታት አንዴት አንዲት ቃል ሳይተነፍሱ ቀሩ በሚል ብዙዎች ተገርመዋል። ፕሮፌሰሩ ከደርግ ወንጀል ጋር ተባባሪ መሆናቸውን በተመለከተ ዝምታን መርጠው እስካሁን አሉ ። ደርጉ ያን ሁሉ ሕዝብ ሲጨፈጭፍና ሽብር ሲያካሂድ ከፕሮፌሰሩ የተሰማ ተቃውሞ አልነበረም። የሰብዓዊ መብት ድርጅት ማቋቋሙ ቢቀርባቸውም በትንሹም ቢሆን የተነፈሱት የተቃውሞ ድምጽ አልነበረም ። ኮብልለውም ደርጉን ማጋለጥ ይችሉ ነበር ፣ አላደረጉትም። ተቃውሞ ያላሰሙት ከዚያ አገዛዝ ጋር ሰምረው ስለነበር እንደሆነ የማያውቅ የለም ። ዛሬም ቢሆን ጥፋታቸውን ከማመን ይልቅ ሌሎችን ሊከሱ መጣራቸውን የአሁኑም መጽሃፋቸው ቁልጭ አድርጎ ያሳያል ።

ፕሮፌሰር መስፍን ከአሜሪካ ጋር ጥብቅ ግንኑነት እንዳላቸው ሲነገር ዓመታት አልፈዋል ። በባዶ አይደለም ፤ መሰረተ ቢስ ነው ማለትም አይቻልም ። ደርግ ሊወድቅ ሰሞን ወደ አሜሪካ ብቅ ብለው የሽማግሌ መንግስት የሚል ደርግን አደናጋሪና የተኪን ሂደት አበላሽ ሀሳብ ይዘው መጥተው ያደረሱት

ጉዳትና ለወያኔ የሰጡትንም ጠቀሜታ ራሳቸውም የሚክዱ አይመስለኝም ። ይህን በተመለከተ አንድ ታዛቢ ይህንን ጽፏል-- *" በ1982 በአ.አ. ዩኒቨርሲቲ በተካሄደው 11ኛው የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ዓለም አቀፍ ጉባዔ ላይ ተሳትፊ ነበር፡፡ በዚህ ጉባዔ መስፍን አንድ " trusteeship government…` የሚል የጥናት ወረቀት እንሚያቀርብ ፕሮግራም ተይዞለት ነበር፡፡ አዳራሹ ገብተን ያጋጠመን ግን "የሽማግሌዎች የእርቅ መንግስት" የሚል ርእስ ሲሆን እራሱ እንደተናገረው ወያኔ እየገሰገሰ በመሆኑ ያጠናውን ወረቀት ትቶ ሌሊት ያሰላሰለው ሀሳብ መሆኑን ገና ሲናገር እሽቱ ጮሌ የመጀመሪያው አዳራሹን ለቆ ወጪ ሆነ፡፡ ከዛም ብዙዎች ወጡ፡፡ በዚህ መሀል ፕሮፍሰር ስቬን ሩቤንሰን ከተሰብሳቢው መሀል ተነስተው "መስፍንን በደንብ አውቀዋለሁ፡፡ መስፍን አርባ ዘጠኝ ለአንድ ቢሸነፍ መሸነፉን የማይቀበል ነው፡፡ መስፍን በዲሞክራሲ የማያምን ሁሌም እኔ ያልኩት ካልሆነ ብሎ ግትር የሚል ነው" ብለው በተሰብሳቢው ፊት አቅልለውታል፡፡*

ለነገሩማ ወያኔ ከጫካ ራዲዮኑ ፕሮፌሰሩን አብጠልጥሎ ሰድቧቸው ነበር ። ግን በአሜሪካ ሴራ የሰላም ውይይት በተባለው ጊዜ በአብዱል አባ ቦራ ደርሶ መልስ ተገዛልኝ ብለው ወደ ለንደን ዘልቀው ከመለስም ከኢሳያስም ጋር እነ እንድርያስንና አብዱልን ይዘው ተገናኝተዋል ። በወቅቱ ለንደን የነበሩት እነ ፕሮፌሰር ማሞ ሙጬም ይህን አሉታዊ ሚናቸውን በጽሁፍ አጋልጠዋል በጊዜው ። በምስጢር ወያኔን ደጋፊ ስብሰባ ፕሮፌሰሩ ጠርተው ልጆቼ ናቸው ብለው ወያኔን ሲያቆላምጡ ሀገር ወዳድ የለንደን ነዋሪዎች በግድ ገብተው አራውጠዋቸዋል። ። ከዚያ በኋላማ ለ ሀ ን ተከተለ ነው የሆነው ነገሩ ሁሉ ። ወደ አዲስ አበባ ገብተው ከመለስ ዜናዊ፤ ከመኮንን ቢሻው፤ ከእንድርያስ እሸቴ ጋር ውይይት በሚል ለወያኔ ያልነበረውን ገጽታ ከመስጠታቸውና ያለን ሕዝብ የለም ከማለታቸው ባሻገር ኢዴሀቅን ደም የጠማው ወዘተ ብለው አውግዘው ወያኔን አጅበዋል ። ወያኔ ከሻዕቢያ ጋር ሆኖ ሽግግር ባለው ጉባኤስ አዛውንቱ ፕሮፌሰረ አስራት ለብቻቸው ሲጋፈጧቸው ፕሮፌሰር መስፍን የት ነበሩ ? ይህን በተመለከተ ሊላ ታዛቢ ደግሞ ይህን አስፍሯል፡ *"መስፍን በተደጋጋሚ የፐሮፌሰር አስራትን ጥረት አምርሮ ይተች ነበር፡፡ አስራት የአማራ ድርጅት ያቋቋሙት በወቅቱ በአማራው ላይ ይደርስ የነበረውን እልቂት ለመጋተር እንደነበር አይዘነጋም፡፡ እሱ የእነልደቱ አማካሪ በመሆን ኢዴፓን መስርቶ የፖለቲካ ቁማር ቆመረ፡፡ እሱ ቀስተደመና የሚባል የሆያ ሆዬ ድርጅት መስርቶ ዳግም ቆመረ፡፡ መስፍን አንድነት የሚባለውን ድርጅት ለማፍረስ ከሁለት አመት በላይ ፍርድ ቤት ሲሟገት ትግሉ ላያ ይህ ነው የማይባል ውሀ ቸልሶበታል፡፡ የሚመሰርታቸው ድርጅቶችን ከእነእንድርያስ ጋር እየተማከረ በመሁኑ ከቱሻ ድርጅትነት መሻገር አልቻሉም፡፡ ሰማያዊ ፓርቲንም የመሰረትኩ እኔ ነኝ ማለቱም አይዘንጋ ፡፡"*

በታሪካቸው መቸም ቢሆን ለስብዓዊ መብት ቆመው የማያውቁት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ለምን በወያኔ ጊዜ ድንገት የሰብዓዊ መብት ተቋም አቋቋሙ? ለዚህ አቢይ ጥያቄ አዎንታዊና የምስጋና መልስ የሚሰጡ እንዳሉት ሁሉ ይህ ድርጊት ጠንካራ የሆነ የሰብዓዊ መብት አስከባሪ ኮሚቴ እንዳይቋቋም ለማገድ ወይም ለመግታት ነው የሚሉም አሉ ። አንድ ታዛቢ እንደሚከተለው ጽፏል፡

*"የሰብአዊ መብት ጉባዔ የማቋቋም ሀሳብን ያማከረው አሰፋ ጫቦ መሆኑን ተናግሯል፡፡ ሀሳቡን በተግባር ላይ ለማዋል ያማከረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደመኛ ጠላት የሆነውን እንድርያስ እሸቴን ነበር፡፡ ከእንድርያስ ጋር የሚገናኙትበትን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ መሸታ ቤት ነው፡፡ መቸም በእንድርያስ አማካሪነት መልካም መመኘት አይቻልምና ነው፡፡ "*

ተዓማኒነትም አለው ። ፕሮፌሰር መስፍን ኢሰመጉን እንደ ግል ሀብታቸው ከመጠቀማቸው ባሻገር (መግለጫዎችን ሳይቀር ለብቻቸው ያወጡ እንደነበር አብረው የሰሯቸው ገልጸዋል ) አቤቱታ ሲመጣ መረጃ የለንም ብለው ያፍኑ እንደነበርም የተነገረ ጉዳይ ነው ። ፕሮፌሰሩ የስብዓዊ መብት ንቁ አስከባሪ አለመሆናቸውን ደግሞ የታሰሩና ደብዛቸው የጠፋውን ራሳቸው እስካልወደዱ ድረስ በጭራሽ ስማቸውን ሳይጠቅሱ መቆየታቸውን ስንገነዘብ ጉዳዩ ግልጽ ይሆናል ። ከዚህ በተጨማሪ ፕሮፌሰር መስፍን ለወያኔ ድጋፋቸውን በመቀጠል የቆዩ ሲሆን ከወያኔ አፋኝ ጸጥታ ሀላፊ ከክንፈ ገብረ መድህን ጋር ጥብቅ ወዳጅነት መስርተው እንደነብርና ሲሞትም ዛሬ ኢትዮጵያ ትልቅ ሰው አጣች ብለው መናገራቸውን ማስታወስ ይበቃል ። የስብዓዊ መብት ተቋም መሪ እንደመሆናቸው መጠን ከጸጥታና ከፖሊስ ሀላፊዎች ጋር ግንኙነት መኖሩ የሚጠበቅ ቢሆንም የወያኔ የጸጥታ ሹም ክንፈ ይህን አያደርግም፤ጥሩ ሰው ነው፤ ለእኔ ወዳጄ ነው ማለቱ ግን መረን የለቀቀና ምንም ማጠየቂያ የማይገኝለት ነው ። እሳቸው ለወያኔ ተከላካይ መሆናቸውም የኢትዮጵያ አንድነት ግንባር የተገኘ ቀዳዳን ተጠቅሞ ትጥቅ ትግል ሲጀምር መላ ወይስ ዱላ በሚል በሙሉጌታ ሉሌ መጽሄት ላይ ትጥቅ ትግልን የሚያወግዝ ጽሁፍ አቅርበው መገኘታቸው አረጋግጦታል ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከኢትዮጵያ ደመኛ ከስብሃት ነጋ ጋር ጠበቅ ያለ ግንኙነት መስርተዋል መባሉም መረሳት የለበትም ።

ፕሮፌሰር መስፍን ከወያኔ ጋር ሆነው ገና በ1983/1991 በፈረደበት አማራ ላይ ጥይት የተኮሱ ናቸው ። ይህም በ ዩ ቲዩብ ተቀርጾ አለ ። (https://www.youtube.com/watch?v=CmdgqTwSkQY). አሁንም ይህን አቅዋም ማስተጋባት ቀጥለዋል ። ፕሮፌሰሩ ታሪክን ማወላገድ ልምድ ሆኖባቸዋል ። በለንደን ሊያቀርቡት የተነሱት አዲስ መጽሃፋቸው ውስጥ ለምሳሌ የየካቲት 66 ትውልድ የእርስ በርስ መጋደልን

አመጣ ብለው ይወነጅላሉ ። ለደርግም ሽብርና ወንጅል ማጠየቂያ ሊሰጡም ይጫጭራሉ ። ያሳዝናል ። ለመሆኑ በፕሮፌሰሩ ትውልድ  ጊዜ ሰላም ሰፍኖ ነበር ? ከዘመነ መሳፍንት እስከ ዘመነ ወያኔ ድረሰ ሲካሄድ የነበረው ጦርነትና ግድያ ግድያ አልነበረም ማለት ነው ? በአጼው ጊዜ የተሰቅሉትን አርበኞች፤ እነ መንግስቱና ገርማሜን፤የጎጃምን አርሶ አደርና ሌሎችንም የፈጀና በሀይል ያጠቃው የየካቲቱ ትውልድ ነው ማለት ነው ? ፕሮፌሰር መስፍን መረን ለቀዋል ። ጸረ ደርጉን ትውልድ ስለጠሉ ታሪክን እስከ መካድና ማዛባት ተገፍተዋል ። በለንደን ነዋሪ ኢትዮጵያውያን ፕሮፌሰሩን ቢያፋጥጡና በቃዎት ቢሏቸው ምንኛ በበጀ !

ፕሮፌሰር መስፍን ህብረትን ለማፍረስ ቀስተ ዳመና የሚልም ተቋም መመስረታቸውን ፤ ቅንጅትን ለማፍረስ ወይዘሪት ብርቱካንን መሳሪያ ማድረጋቸው ደግሞ የሚታወቅ ነው ። ዶክተር ታዬ ወ/ሰማያት ከርቸሌ ታስሮ ሲሰቃይ አንዴም ብቅ ብለው አልጠየቁትም (ከተሳሳትኩ ልታረም ዝግጁ ነኝ ግን ይህ ነው የተነገረኝ በሚያውቁት ) ። እነ ዶክተር ንጋቱ ኢሰመጉን ሊያድሱ ከማይችሉበት ደረጃ ያደረሱት ና ያዳከሙት ፕሮፌሰር መስፍን ናቸው ። በወያኔ ጽንፈኝነት ወይም ስልት አንዴም ለእስር ቢበቁም ፤ ይቅርታ ጠይቀው ሲለቀቁ በቀር በየአገዛዙ በነጻ የተተዉ ናቸው ። ታዳጊዋን ያመነች በግ ላቱዋን ደጅ ታሳድራለች ይባል የለ ?

ይገባኛል ይህ ጽሁፍ ለጣፊ ወይም አታሚ ካገኘ (?) እንዴት ተደፍረው የሚለው ክፍል ብዙ ጫጫታ እንደሚያሰማ ። ከጻፍኩት ውስጥ ውሸት ወይም ሀሰት ካለ እስቲ ይህ የተባለውን አላረጉም አልሰሩም ብሎ እሰጥ አገባ ይሞግተኝ። ካልሆነ ግን በስድብና ዘለፋ ምላሽ ለመስጠት መነሳቱ ጥቅም የለውም ። የፕሮፌሰር መስፍን የረጅም ዓመታት በአሜሪካ የተደገፈ አሉታዊ ሚና ማብቃት አለበት ። ፕሮፌሰሩ ወዳጅ ካላቸው በቃ ራስዎን ከሁሉም ነገር አርቀው ጡረታ ይውጡ ብሎ ሊመክራቸው ይገባል ። ለምን ከተባለ ደግሞ መረጃ አዘል ተጨማሪ መከራከሪያ ማቅረቡ ከባድ አይሆንም ።

ሀቀኛው ታሪክ ይነገር ። በፕሮፌሰር መስፍንም ተባባሪነት የተረሸኑትም  ነፍሳቸው ትረፍ።